
**Ethiopian Evangelical Baptist Church**
2822 S. Jupiter Road
Garland, TX 75041
**Telephone:** 214-703-0100
**Fax:** 214-703-0161
www.eebc-dallas.org

# የዕብራዊያን መልዕክት




## በኢትዮፕያዊያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሕብረቶች የተዘጋጀ

ማውጫ፡-


1. መግቢያ ............................................................ 1-3
2. አዲስ ኪዳን፡- የእግዚአብሔር መጨረሻ ቃል .................. 4-6
3. የደኅንነት መሪ .................................................... 7-9
4. ከሙሴ የሚበጠው ኢየሱስ ..................................... 10-11
5. ፍጹም እረፍት በኢየሱስ ....................................... 12-13
6. ከአሮን የሚሻለው ኢየሱስ .................................... 14-15
7. በትዕግስት መጠበቅ .............................................. 16-18
8. ከሌዊ የሚበልጠው ኢየሱስ .................................... 19-20
9. የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ........................... 21-22
10. የእውነተኛይቱ ድንኳን አምልኮ ............................. 23-25
10. ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ................................. 26-27
11. ድፍረትህን አትጣል .......................................... 28-29
12. የተመሰከረለት እምነት ....................................... 30-31
13. ታላቅ መስዋዕትን መክፈል ................................. 32-34
14. የእምነት አርበኞች .............................................. 35-36
15. በሕይወታችን እንዳንዝል ..................................... 37-39
16. ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖረን .......................... 40-42

# የዕብራውያን መልዕክት ጥናት

## መግቢያ

ጸሓፊው፡-

የዚህ መልዕክት ጸሓፊ ማንነቱን አልገለጠም፥ ሆኖም ግን በመጀመሪያዎቹ የመልዕክቱ ተደራሲያን ዘንድ የታወቀ ነው፥ መጽሐፉ ለ1200 ዓመታት ያህል
(ከ400-1600 ዓ.ም) “በተለምዶ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ዕብራውያን” በመባል የሚታውቅ ቢሆንም በመጀመሪያዎቹ ምእተ ዓመታት ግን ተቀባይነት አላገኘም ነበር።

የዕብራውያን መልዕክትና የጳውሎስ መልዕክቶች በሚያስተላልፉት ትምሕርቶች መካከል አለመጣጣም አይታይም፥ነገር ግን በልዩ ሁኔታ አጽንዖቶ በሚያደርጉባቸው ጉዳዮችና በአጻጻፍ ስልታቸው መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ።

1. ጳውሎስ በጻፋቸው መልዕክቶች ውስጥ ስሙን ይገልጻል፡ የዕብራውያን መልዕክት ጸሓፊ ግን ምንም ስለራሱ ስም አይናገርም።

2. ጳውሎስ ሲጽፍ ከጌታ እንደተቀብልኩት ይላል፡ የዕብራውያን ጸሓፊ ግን (2፡3) “የሰሙትም ለእኛ አረጋገጡልን ይላል።

የመልዕክቱ ተደራሲያን

መልዕክቱ በመጀመሪያ የተጻፈው ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቀው ለሚያውቁ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ሲሆን፡ ይኸውም ወድ ይሁዲነት በመሳብ ላይ ለነበሩ ወይም ወንጌልን ከአይሁድ እምነት ጋር ለማቀላቀል (ከገላ. 2፡14 ጋር ያነጻጽሩ) ይጥሩ ለነበር ምእመናን ነው። እንዲሁም የዚህ መልእክት ተቀባዮችን አስመልክቶ፡ ለእምነት ታዛዥ ከሆኑት አያሌ ካህናት መካከል የነበሩ ሰዎች (ሐሥ. 6፡7) ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚናገሩም አሉ።

የመልዕክቱ መሪ ሐሳብ

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሐርን ጸጋ ለመግለጥና በእርሱም በኩል ይህ ጸጋ ወደ ሰው እንዲደርስ፡ ፍጹም ወደር የማይገኝለት ብቃት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው

1. ክርስቶስ እንከን የሌለበትና ከሁሉ የላቀ የእግዚአብሔር መገለጥ አድርጎ አቅርቦታል። (1፡1-4)

2. ክርስቶስ ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ተሰጥቶ ከነበረው መገለጥ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚበልጥ ነው።

3. በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ትንቢቶችና የተስፋው ቃሎች የተፈጸሙት ክርስቶስ መካከለኛ በሆነበት በአዲስ ኪዳን ነው።

4. ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ከነበሩት

ሀ. ከነቢያት

ለ. ከመላእክት

ሐ. የአሮጌው ኪዳን መካከለኛ ከነበረው ከሙሴ

መ. ከሊቀ ካህኑ አሮንና ከዘሮቹ ሁሉ የላቀ መሆኑ በግልጽ ተጠቅሶ ይገኛል።

በዚህ መልዕክት ውስጥ "የተሻለ" እና "የላቀ" ለሚሉት ቃላት አቻ የሆኑ ሁለቱ የግሪክ ቃላት ዐሥራ አምስት ጊዜ ስለ ተጠቀሱ፣ መልዕክቱ "የተሻለ መጽሐፍ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ይህ መሪ ሐሳብ በአማኝ ሕይወት እንዴት ተግብራዊ ሊሆን እንደሚገባው በመጽሐፉ ውስጥ በስፋት እንመለከታለን። አሮጌው የአይሁድ ሥርዐት፣ ልዩ በሆነ የክርስቶስ ክህነት ስለ ተተካ፣ ወደዚያ መመለስ ወይም በዚያ ስርዓት መቀጠል፣ ከቶ ሊታሰብ እንደማይቻል ለአንባቢው ተገልጾአል። ከእንግዲህ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ እውነተኛ ወደ ሆነው ወደ ሰማያዊው የእግዚአብሔር መቅደስ መግቢያ ስርየት ወዳገኙበት ወደ ኢየሱስ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት ብቻ መመልከት ይኖርበታል።

አማኞች ወደ ፊት በመሄድ የሚታገላቸውን ፈተና በጌታ በመወጣት፣ የጀመሩትን መንፈሳዊ ውጊያ ጸንተው መቀጠል አለባቸው። አለበለዚያ በምድረ በዳ የነበረው ዐመፀኛው የእስራኤል ሕዝብ የደረሰበት ዐይነት ቅጣት ሊደርስባቸው ይችላል።

<u>ጥናት አንድ</u>

## <u>አዲስ ኪዳን - የእግዚአብሔር የመጨረሻ ቃል።</u>

**<u>የምንባብ ክፍል ዕብ. 1፡14፣2፡1-4</u>**

**<u>መግቢያ፡</u>** የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር የድነትን (Salvation) የተስፋ ቃል በተለያየ ጊዜ እና ሁኔታ ሰጥቶአል። ይህ የደህንነት ተስፋ ቃል ብሉይ እና አዲስ ኪዳን በመባል ይከፈላል። በዛሬው ጥናታችን የእነዚህን ሁለት ኪዳኖች ልዩነት እንመለከታለን።

**<u>ዓላማው፡-</u>** ምንም እንኳ ብሉይ ኪዳንን የሰጠው እግዚአብሔር ቢሆንም ፣ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር የመጨረሻ ኪዳን በመሆኑ፣ እውነተኛ ደህንነት የሚገኘው በአዲስ ኪዳን እውነት ብቻ መሆኑን ለመገንዘብ።

1. በቁጥር 1-2 መሰረት፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረበት መንገድ በስንት ይከፈላል?

    - እነዚህስ አባባሎች ምንና ምንን ያመለክታሉ?

2. በቁጥር 1 መሰረት ፣ እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን የሰጠው "በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና... በነብያት" አማካኝነት ነው።

    - ይህ ምን ማለት ይመስልሃል?

3. በቁጥር 2 ላይ እንደምናየው እግዚአብሔር አዲስ ኪዳንን የሰጠው " በልጁ" በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነው።

    - በቁጥር 2-3 ላይ በመመርኮዝ ለክርስቶስ የተሰጠውን ስምና ማዕረግ ዘርዝር።

4. ከቁጥር 1-3 ያለውን በመመርኮዝ፣ ከብሉይ ኪዳን እና ከአዲስ ኪዳን የትኛው ይበልጣል? ለምን?

5. አሁን ባለንበት ዘመን አንዳንድ የሀይማኖት ሰዎች እንደ ብሉይ ኪዳን ስርዓት ለመኖር ሲሞክሩ ይታያል።

    - አሁን ካነበበው ክፍል በመነሳት፣በብሉይ ኪዳን ስርዓት የማንመላለስበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?

6. ጌታ በአዲስ ኪዳን አገልግሎት ኃጢአታችንን አንፅቶ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡን ቁጥር 3 ይነገረናል።

- የጌታ አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን አገልግሎት ጋር ሲወዳደር ስለ አዲስ ኪዳን ጥራትና ብቃት ምን ይነግረናል?

7. ከቁጥር 4-14 ባለው ክፍል አዲስ ኪዳንን ያስገኘውን ጌታ ከመላዕክት ጋር ያወዳድራል።

    - በዚህ ክፍል መላዕክትን መጥቀስ ለምን ያስፈለገ ይመስልሃል?

    - (ሐዋ. 7፡38 ይመልከቱ።) (ለአስጠኚው፡- ብሉይ ኪዳን በነብያት በኩል እንደተሰጠ፣ በመላዕክትም በኩል ተሰጥቶአል።)

8. በቁጥር 4 መሰረት ጌታ የተሰጠው ስም ከመላዕክት (መልዕክተኞች) የሚበልጥ እንደሆነ ይነግረናል ።

    - ቁጥር 5ን በመደገፍ ለጌታ የተሰጠው ስም ማን ነው?

9. ቁጥር 5 እና 6ን እንዲሁም ቁጥር 7 እና ከ8-14 ያሉትን በማወዳደር ጌታ ከመላዕክትስ እንዴት ነው የሚበልጠው?

    - ከም.2፡2-3 በጌታ ያለማመንና የአዲስ ኪዳንን እውነት አለመቀበል ቅጣት ከባድነት እንዴት ነው የተገለፀው?

    - ከም.2፡3-4 በመመርኮዝ ለምንድነው አዲስ ኪዳን የበለጠ ክብደት እንዲኖረው ያደረገው?

10. እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን ከሰጠ በኋላ አዲስ ኪዳንን በልጁ በኩል እንደገና ለመስጠት ለምን አስፈለገው?

    - ይህስ እውነት ስለ መዳንህ ጌታን ይበልጥ እንድታመሰግንና እንድታገለግል እንዴት ሊረዳህ ይችላል?

## ጥናት ሁለት

## የደኅንነት መሪ

**የዕብራዊያን 2፥5-18**

**መግቢያ** ፡- በዛሬው ጥናታችን በኃጢአት ምክንያት ክብሩንና ስልጣኑን ተገፎ የነበረውን ሰው በክርስቶስ አማካኝነት እግዚአብሔር እንዴት ወደ ቀደመው ክብሩ እንደመለሰው እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር እንዴት የሰውን ልጅ ከኃጢአት እስራት ነፃ አውጥቶ ለከበረና ለድል ሕይወት እንደጠራው ለመገንዘብ።

1. ፀሐፊው በቁ.5 ላይ ስለ የትኛው ዓለም ነው የሚናገረው?
   - የሚመጣውስ ዓለም የትኛው ነው?
2. ከቁጥር 6-8 የሚናገረው ስለማን ነው?
   - እግዚአብሔር አደረገ ብሎስ የዘረዘራቸው ነጥቦች ምንድናቸው?
3. በቁ.9 ላይ ክርስቶስ የጫነውና፥ የጫነበትስ ምክንያት ምንድነው?
4. ዳዊት በመዝሙሩ እግዚአብሔር የሰውን ዘር እንዳሰበና እንደራራለት አይቶ፣ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድን ነው ብሎ ዘምሯል።
   - እግዚአብሔር የሰውን ዘር የጎበኘውና ያሰበው እንዴት ነው?
   - ይህ እውነት ስለ ደህንነት ምን ያስተምረሃል?
5. በአንድ በኩል እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ ለአዳምና ለሔዋን እንዳደረገው (ዘፍ 1፥28) ፣ ሁሉን ከእግሮቹ በታች እንደሚያስገዛለት ዳዊት ዘምሯል። በሌላ በኩል ግን ዛሬ ሁሉ ነገር ሲገዛ አናይም ይለናል።
   - የዚህ አባባል ትርጉም ምን ይመስልሃል ? (ቁ.9 እና 1፥3 ተመልከት)
6. በቁ.10-13 የሚቀደሰው ኢየሱስ፥ የሚቀደሱት አማኞች ከአንድ ከእግዚአብሔር እንደሆኑ ይነግረናል።
   - ቀጥሎ የተጠቀሱት 3 ጥቅሶች ይህንን ሃሳብ እንዴት ይገነባሉ?
7. በቁ.14-15 ባለው ሃሳብ መሠረት ጌታ ሰው መሆን ለምን አስፈለገው? (ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች ተሰጥተዋል።)

8. ጌታ በሞት ላይ ስልጣን የነበረው ዲያቢሎስን የሻረው እንዴት ነው?

9. ዲያቢሎስ በሞት ላይ ስልጣን የነበረው እንዴት ነው?

10. ጌታ የሰውን እንጂ የመላዕክትን ዘር ይዞ እንዳልመጣ ቁ.16 ይነግረናል።

- ይህ እውነት እግዚአብሔር የሚመጣውን ዓለም ለመላዕክት ሳያስገዛ፣ ለሰው ልጅ ሊያሰጋዛ ስለቻለው ምክንያት ምን ያስገነዝብሃል?

11. በቁ.17 ላይ የጌታ ስጋ ለብሶ መምጣት ለምን እንዳስፈለገ ሌላ የሚሰጠው ምክንያት ምንድነው?

12. ጌታ ኢየሱስ ስጋ ለብሶ ባይመጣ ኖሮ ሊቀ ካህናት እንዳይሆን የሚከለክለው ምን ነገር ይኖራል ብለህ ታስባለህ? ( በተጨማሪ ዕብ 5፡1-3 ይመለከታሉ)

13. ጌታ እንደኛ በነገር ሁሉ የመፈተኑ እውነት፣ ለእኛ የሚያስቀረልን ምን ጥቅም አለው?

14. ጌታ ከኃጢአት እስራት ነፃ ያወጣን ለከበረና ለድል ሕይወት እንደሆነ መረዳትህ ምን ይጠቅመሃል?

## ጥናት ሦስት

# ከሙሴ የሚበልጠው ኢየሱስ

**የምንባብ ክፍል ዕብ. 3-19**

**መግቢያ፣** በዚህ ምዕራፍ ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ላይ የታመነ አገልጋይ ሲሆን ኢየሱስ ደግሞ የታመነ ልጅ እንደሆነ የተፃፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፣** በየዕለት ኑሮአችን የጌታን የበላይነት በማወቅ፥ እስራኤላዊያን በሙሴ አመራር ላይ በማጉረምረማቸው እንደጠፉ፥ እኛም የእምነታችን መሪና መሥራች የሆነውን ኢየሱስን ብንቃወም፥ የበለጠ ፍርድ እንዳለ ተገንዝበን በማስተዋልና በመታዘዝ እንዴት መኖር እንደሚገባን ለመረዳት።

1. በቁጥር 1 ላይ ፀሐፊው የመልዕክቱን ተቀባዮች በሦስት ገላጭ ቃላት ይገልፃቸዋል።
   - እነዚህ ሦስት ሃሳቦች ምን እንደሆኑና ትርጉማቸውን ግለፅ?
2. በቁጥር 1 ላይ ፀሐፊው ኢየሱስን የገለፀባቸው ሁለት የአገልግሎት ዓይነቶች ምንና ምን ናቸው?
3. ከቁ.2-6 በሙሴና በኢየሱስ መካከል ያለው ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዴት ነው የተገለፀው?
   - ሙሴንና ኢየሱስን ያወዳደረው ለምን ይመስልሃል?
4. ከቁ.7-11 ባለው ክፍል የእስራኤላዊያን የ40 ዓመታት የምድረበዳ የማጉረምረም ታሪክ ለምን የተጠቀሰ ይመስልሃል?
   - ከዚህስ የምንማረው እውነት ምንድነው?
5. በቁ 12 ላይ ፀሀፊው የመልዕክቱን ተቀባዮች እንዲጠነቀቁ ያሳሰባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው?
6. “ዛሬ ተብሎ ሲጠራ” (3፥13) የሚለው ቃል በዚህ መጽሐፍ በመደጋገም ተገልጿል።
   - የተደጋገመበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
7. ከቁ.16-19 ፀሐፊው የጠየቃቸው አምስት ጥያቄዎች ምንና ምን ናቸው?

8. የእሥራኤላዊያን የምድረበዳ ውድቀት ለመልዕክቱ ተቀባዮች መፃፍ ለምን ያስፈለገ ይመስልሃል?

9. በቁ.19 መሠረት እስራኤላውያን ወደ እረፍት እንዳይገቡ የተከለከሉበት ዋነኛው ምክንያት ለምን ይመስልሃል?

9. ዛሬስ በአዲስ ኪዳን ክርስቶስን አለማመን ምን ሊያስከትል የሚችል ይመስልሃል?

10. ማጉረምረም በሰው ሕይወት ሊያመጣ የሚችለውን ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ተገንዝበሃል?

11. አሁን አንተ የክርስቶስ ቤት መሆንህን ማወቅህ ስላንተ ያለህን አመለካከት እንዴት ሊቀይረው ይችላል?

<u>ጥናት አራት</u>

## <u>ፍፁም ዕረፍት በኢየሱስ</u>

**<u>የምንባብ ክፍል ዕብ. 4፡1-14</u>**

*<u>መግቢያ፡-</u>* ኢያሱ እስራኤላዊያንን ወደ ተስፋው አገር ቢያስገባቸውም ከነዓን ፍፁም የማረፊያ ስፍራ አልሆነላቸውም። ፀሐፊው ይህንን እውነት ከጠቀሰ በኋላ ፍጹም ዕረፍት በጌታ ብቻ መሆኑን የገለፀውን እውነት እንመለከታለን።

*<u>ዓላማ፡</u>* የኢያሱን አስተዋፅኦ ከጌታ ጋር በማወዳደር፥ በጌታ ያገኘነውን ፍፁም ዕረፍት ለማመስገንና ላገኘነውም ዕረፍት አጥብቀን እንዴት መጠንቀቅ እንዳለብን ለመገንዘብ።

1. በ4፡2 ላይ የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር ስላልተዋሃደ አልጠቀማቸውም የሚለው እነማንን ነው?
   - ከምዕራፍ 3 ጋር በማወዳደር ተወያዩበት።
   - በአሁኑ ጊዜ ይሄ ከእኛ ጋር ሊዛመድ የሚችለው እንዴት ነው?
2. እስራኤላውያን እግዚአብሔር ወደ ተናገራቸው ስፍራ ሊገቡ ያልቻሉበት ምክንያት ለምንድ ነው?(ቁጥር 6)
3. "ኢያሱ አሳርፏቸው ቢሆን ኖሮ" ከሚለው ከመዝሙረ ዳዊት "ዛሬ ተብሎ ሲጠራ" ከሚለው ጋር ፀሐፊው ለምን ያገናኘው ይመስልሃል?
4. እሥራኤላዊያን በምን መንገድ ነው ለእኛ ምሣሌ የሚሆኑት? (ቁጥር11)
5. የእግዚአብሔር ቃል የተገለጠባቸውን ሦስት ባህሪያት ተወያዩበት(12)
6. የእግዚአብሔር ቃል የሚነካው ምናችንን ነው? (ቁጥር 12)
   - ከዕረፍትና ከአለመታዘዝ ቀጥሎ ፀሃፊው ይህንን ሊናገር ለምን አስፈለገው?
7. በእግዚአብሔር ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተ ነው የሚለውን እንዴት ትረዳዋለህ?
8. በቁ4፡14 ኢየሱስ የተገለጠባቸውን ሦስት ባህሪያት ጥቀስ?
9. ኢየሱስ በድካማችን ሊራራ የሚችል ሊቀ ካህን የሆነው ለምንድነው?
   - ከዚህስ አባባል የምትማረው እውነት ምንድነው?

10. ምህረት በሚያስፈልገን ጊዜ ወዴት ነው መቅረብ ያለብን?
    - የምንቀርበውስ በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው ? (ቁጥር 16)

11. ስለዚህ ከጌታ ዘንድ ዕረፍት እንዲሆንልህ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?

11.ስለ እግዚአብሔር ቃል ብርቱነት መረዳትህ ለቃሉ ያለህን አክብሮት እንዴት ሊጨምርልህ ይችላል?

# ጥናት አምስት

# ከአሮን የሚሻል ኢየሱስ

**የምንባብ ክፍል ዕብ. 5፥1-14**

**መግቢያ፦**

የአሮን ሊቀ ክህነት ከክርስቶስ ጋር ያለውን ተመሣሣይነትና ልዩነት በዚህ ክፍል እንዴት እንደሆነ እንመለከታለን።

**ዓላማ፦**

በሚሻል ሊቀ ክህነት የተገለጠውን ጌታ በጠለቀ ለማወቅና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዴት ይበልጥ መጠንከር እንዳለብን ለመገንዘብ።

1. ከቁ.1-4 ባለው ክፍል መሠረት የሊቀ ካህኑ አገልግሎት ምንድነው?
    - ለሌሎች የሚራራበት ምክንያት ለምንድነው?
    - የሚያቀርበው መሥዋዕትስ ለማን ነው?
    - ከክርስቶስ አገልግሎትስ ጋር የሚገናኘውና የሚለያየው እንዴት ነው?
2. ከቁ 4-10 መሠረት ክርስቶስ ልመና ያቀረበው ለምንድነው?
    - ልመናውን ያቀረበው በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው?
    - ኢየሱስ "ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ" የሚለውን እንዴት ትረደዋለህ?
    - የጌታስ መታዘዝ ያስገኘው ውጤትስ ምንድንነው?
3. ፀሐፊው የመልዕክቱን ተቀባዮች በቁጥር 11 ላይ እንዴት ይገልፃቸዋል?
    - እንዲህ ብሎ ሊናገር ያስቻለው ምክንያት ምንድነው?
    - በአሁንስ ጊዜ እኛስ እንደዚህ ልንሆን እንችላለን? በምን መንገድ?
4. ከቁ 12-13 ፀሃፊው የሚገስፃቸው ምን ብሎ ነው?
5. በቁ.14 ላይ ጠንካራ ምግብ የሚመገቡ ሠዎች ባህሪያትን ተወያዩበት
6. በአጠቃላይ ጌታ ከአሮን የተሻለ ሊቀ ካህን ሊሆን የቻለው ምንን በመታገሱ ነው?

- **መታዘዝስ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ይህ ክፍል ያስተምረሃል?**

## ጥናት ስድስት

## በትዕግሥት መጠበቅ

**የምንባብ ክፍል ዕብ. 6፥1-20**

**መግቢያ፡-**

ትዕግስት በሕይወት ጎዳና ውስጥ ፈታኝ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነገር ነው። ሆኖም ግን ትዕግስት ከሌለ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር የወሰነልንን ነገር ለመጨበጥ አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህም የዛሬው ጥናታችን የክርስትና ጉዞአችን እንዴት መሆን እንዳለበት የተፃፈውን እንመለከታለን

**ዓላማ ፡-**

እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ በመሆኑ እኛም በሕይወታችን ሁሉ ፈቃዱን ለመፈፀም ብንነሳ የተስፋ ቃሉ እንዴት በሕይወታችን እንደሚፈጸም ለመገንዘብ።

1. ከቁ.1-3 ፀሐፊው የሚመክራቸው ስለ ምንድነው?
   - ምን ማለት እንደሆን በዝርዝር ተነጋገሩበት።
2. ከቁ.4-5 በዚህ ክፍል የተገለጡት ሰዎች በአንድ ወቅት በሕይወታቸው የተለማመዱት ነገር ምንድነው?
3. በቁ.6 መሠረት እንደነዚህ ያለውን ሰው ወደ ንስሃ ማምጣት የማይቻለው ለምን ይመስልሃል? (ዕብ፥10፡25-31 ያለውን ያወዳድሩ)
4. ከቁ.7-8 የተሰጠው ምሣሌ ምንድነው?
   - ይህስ ምሣሌ እላይ ከተገለፀው ሃሳብ ጋር እንዴት ይገናኛል?
5. በቁ.9 ላይ የዕብራውያን ሰዎች ግን እንደሚጠፉና ንሰሃ እንደማይገቡት ሰዎች ሳይሆኑ፣ ደህንነትን የሚወርሱ እንደሆኑ ይገልፃል።
   - ቁ.10 ፀሐፊው በዚህ ነገር እርግጠኛ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድነው?
6. ከቁ.10-12 የያዘው ምስጢር (ትርጉም) ምንድነው?
   - የተሰጠውስ ተስፋ ምንድነው?

7. እግዚአብሔር የምንሰጠውን አገልግሎት፣ ለሰዎች የምናሳየውን ፍቅርና መልካም ስራ የማይረሳ መሆኑ መረዳትህ አንተን ምን እንድታደርግ ያነሳሳሃል?

  - በጌታ ታምነው በፍቅርና በመልካም ስራ እያገለገሉ በትዕግስት የሚጠብቁት የሚያድን መሆኑስ መገንዘባችንስ?

8. ከቁ.9-10 በትዕግስትና በጽናት ስለ መጠበቅስ ምን ያስተምረናል?

9. ከቁ.11-12 እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል እስኪፈጸም ድረስ እንዴት እንዲተጉ ነው የሚመክራቸው?

10 . ቁ.13-14 ላይ አብርሐም በትዕግስት ስለመጠበቅ እንደ ምሳሌ ተጠቅሷል።

  - አብርሐም የተሰጠውን የተስፋ ቃል ያገኘው እንዴት ነው?

12. አብርሐም እግዚአብሔር ልጅ እሰጥሃለሁ ብሎ ቃል ከገባለት በኋላ 25 ዓመት ታግሶ ጠብቋል።

  - አብርሐም ይህንን ሁሉ አመት በትዕግስት እንዲጠብቅ ያስቻለው ምክንያት ምንድነው? (ዕብ.10፡23 ይመልከቱ)

13. ከቁ.17-20 እግዚአብሔር ቃሉን የማያጥፍ እና ለአማኞች የሰጠውን ተስፋ የማይረሳ መሆኑን ለማሳየት ያደረገው ነገር ምንድነው?

13. ወደ ንስሃ ለመመለስ አስቸጋሪ መሆኑን መረዳትህ ከምን እንድትቆጠብ ይረዳሃል?

14. መጠበቅስ ብድራት እንዳለው መገንዘብህ ምን ማድረግ እንዳለብህ ያስገነዝብሃል?

## ጥናት ሰባት

# ከሌዊ የሚበልጥ ኢየሱስ

**የምንባብ ክፍል ዕብ. 7፡1-28**

***መግቢያ፡-***

ጌታ በዚህ ክፍል ጌታ እንደ መልከ ጼዲቅ የክህነት አገልግሎት ምሳሌና ከአሮንና ከሌዋዊያን አገልግሎት የበለጠ አገልግሎት እንዳለው የተጻፈውን እንመለከታለን።

***ዓላማ፡-***

ጌታ በብሉይ ኪዳን ከነበረው የክህንነት አገልግሎት የበለጠ አገልግሎት እንዳለው ለመረዳትና ይህንን ትልቅ አገልግሎትም በታማኝነት መፈጸም እንዳለብን ለመገንዘብ።

1. በቁ.1-3 ባለው መሰረት መልከ ጼዲቅ ማን ነው? ዘፍ.14፡17-20
   - የስሙስ ትርጓሜ ምንድነው? "2"
   - `ስለ መልከ ጼዲቅ የተነገረው ምንድነው? "3"
   - ከጌታ ኢየሱስ ጋር የሚመሳሰለውስ እንዴት ነው?
2. ከቁ.4-10 ያለውን በመመልከት
   - መልከ ጼዲቅ ከአብርሐም ይልቅ የከበረ ያደረገው ምንድነው? "4"
   - ከሌዌስ እንዲበልጥ የሚያደርገው ምክንያትስ? "5-10"
3. እግዚአብሔር በመዝ. (110፡4) ላይ ስለ ጌታ ክህንነት ሲናገር " አንተ እንደ መልከ ጼዲቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ" ብሎአል።
   - ጌታ እንደ ሌዌ ክህነት ሳይሆን እንደ መልከ ጼዲቅ ካህን መሆን ለምን አስፈለገው? (ቁ.11 ይመልከቱ)
4. በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሊቀ ካህናትም ሆኑ ካህናቱ በሕጉ መሰረት ሊሾሙ ይገባቸዋል።
   - ከቁ.15-19 ያለውን በመመልከት የጌታ ሹመትና አገልግሎት ከሌሎቹ የሚለየው እንዴት ነው?
5. ከቁ.20-25 ጌታ እንደ መልከ ጼዲቅ ያለ ካህን በመሆኑ ከሌዌ አገልግሎት የሚበልጥ መሆኑን ለማሳየት ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

6. ከቁ.26-28 ጌታ በብሉይ ጊዜ በምድር ከነበሩት ካህናት የተለየ የሚያደርገው እንዴት ነው?
   - በእያንዳንዱ ሃሳብ ላይ ተወያዩበት።

7. ከዚህ በላይ ያጠናነውን ክፍል በመመልከት

   - ስለ ጌታ ሹመትና አገልግሎት የተረዳኸው ምንድነው?

   - ይህን ማወቅህ፥ ይበልጥ ጌታን ለማምለክም ሆነ ለማገልገል እንዴት ሊረዳህ ይችላል?

## ጥናት ስምንት

## የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ

**የምንባብ ክፍል ዕብ. 8፥1-13**

**መግቢያ፦** የኢየሱስ የሊቀ ካህንነት አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን አገልግሎት እንዴት የላቀ እንደሆነ የተፃፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፦** የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህን (ክርስቶስ) በእውነተኛይቱ ድንኳን ውስጥ ስለእኛ የሰጠውንና አሁን እየሰጠ ያለውን አገልግሎትን ምን እንደሆነ ለመገንዘብ።

1. ከቁ.1-2 ሊቀ ካህኑ የተቀመጠው በየት ነው?
   - የአገልግሎቱስ ሥፍራ የት ነው?
   - ይህ ሊቀ ካህን ከሌሎቹ ሊቀ ካህናት የሚለይው እንዴት ነው?
2. ከቁ.3-5 የሊቀ ካህናት አገልግሎት ምንድነው?
   - የሙሴ ድንኳን ምሣሌነት የሚያስተምረን ምንድነው?
3. ከቁ.7-8 የመጀመሪያው ኪዳን ሊቀየር ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው?
4. ከቁ.9-10 ቀድሞ እንደገባሁት ኪዳን አይደለም ብሎ የዘረዘራቸው ነጥቦች ምንድናቸው?
5. ከቁ.10-13 የሚሻለው ኪዳን ያስገኘው በረከትና ውጤት ምንድነው?
6. ሕጉ በድንጋይና (በብሉይ) በልብ (በአዲስ) ላይ መጻፉ የሚያመጣው ልዩነት ወይም ውጤት ምንድነው ነው?
   - ሕጉ በልብ ውስጥ ተፃፈ ሲባል ምን ማለት ይመስልሃል?
7. ቁ.11 ከ1ኛ.ዮሐ.2፥ 20 እና 27 ጋር እንዴት ይመሳሰላል?
8. ኢየሱስ የእውነተኛይቱ ድንኳን ሊቀ ካህን የመሆኑ እውነት ስለ አገልግሎትና ስለ ሕይወት ያለህን አመለካከት እንዴት ይቀይረዋል?

# ጥናት ዘጠኝ

## የእውነተኛይቱ ድንኳን አምልኮ

**የምንባብ ክፍል ዕብ. 9፡1-13**

**መግቢያ፡-** በዚህ ክፍል ጸሐፊው ሁለቱን ኪዳናት እያስተያየና እያነጻጸረ አዲሱ ኪዳን እንዴት የተሻለ እንደሆነ የፃፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን ለማምለክ በክርስቶስ ፍፁምና ነፃ የሆነ ሕይወትን እግዚአብሔር እንዴት እንደሰጠን ለመገንዘብ።

1. ከቁ.1-5 ፊተኛይቱ ድንኳን ስንት ክፍሎች አሉት?
    - እነዚህ ሁለት ክፍሎች ምን በመባል ይታወቃሉ?
    - በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት እቃዎች ምንድናቸው?
    - ምሣሌነታቸውስ ምን ይመስልሃል?
2. ከቁ.6-7 ካህናቱና ሊቀ ካህናቱ የሚያገለግሉት በየትኛው ክፍል ነው?
    - በድንኳኑ ውስጥ አገልግሎታቸውንስ የሚያከናውኑት እንዴት ነው?
3. የቁ.8 ትርጉም ወይም አባባል ምን ይመስልሃል?
4. ከቁ.10 የፊተኛይቱ ድንኳን አገልግሎት ያላመጣው ለውጥ ምንድነው?
    - ህሊናን ፍፁም ያላደረገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
5. ከቁ.11-13 ክርስቶስ ወዴት ነው የገባው?
    - የገባውስ ምንን ይዞ ነው?
    - ይሄ ከፊተኛይቱ ድንኳን አገልጋዮች የሚለይበት ዋና ምክንያት እንዴት ነው?
6. የቁ.14 እና 10 ልዩነት እንዴት ትመለከተዋለህ?
7. ከቁ.15 እርስትን እንዲቀበሉ ክርስቶስ ያደረገው ምንድነው?
8. ከቁ.16-23 በመመልከት ኑዛዜ ምንድነው?

- በዚህ ክፍል ስለ ኑዛዜ ለመናገር ያስፈለገው ምክንያት ምንድነው ?
- ኑዛዜውስ ከክርስቶስ ጋር የሚገናኝበት ሁናቴስ እንዴት ነው?

9. ከቁ.24 ክርስቶስ የገባውና የገባበት ምክንያት ምንድነው?

- ቁ.25 ክርስቶስስ ከሌሎቹ ሊቀ ካህናት የሚለይበት ዋና ምክንያት እንዴት ነው?
- ቁ.26 እንደ ሌሎቹስ ሊቀ ካህን ቢሆን ኖሮ ምን ማድረግ ነበረበት?

10. ቁ.27 ሰው በሕይወቱ የተወሰነበት ሁለት ነገር ምንድነው?

- ቁ.28 ከዚህ በላይ ካለው ሃሳብ ጋር የሚመሳሰልበትና የሚለያይበት መንገድ እንዴት ነው?

11. ይህ ክፍል እግዚአብሔር ለእኛ ስለ አደረገው መልካም ነገር ምን ያስተምረናል?

12. እግዚአብሔርን ለማምለክ እንድንችል ፍፁም አእምሮ ተሰጥቶናል ይለናል።

- በዚህ እውነት መሰረት እግዚአብሔርን ለማምለክ ፍፁም ህሊና አለህ?
- የለኝም የምትል ከሆነስ ለምን ይመስልሃል?

<u>ጥናት አስር</u>

# <u>ወደ እግዚአብሔር መቅረብ</u>

<u>የምንባብ ክፍል ዕብ. 10፡1-25</u>

<u>መግቢያ</u>፡- ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንዳቀረበንና በተጨማሪም ከእያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔር ምን እንደሚጠብቅ እንመለከታለን።

<u>ዓላማ</u>፡- እያንዳንዱ አማኝ ወደ እግዚአብሔር ለመቀረብ ፍፁም ድፍረት በክርስቶስ እንዳገኘና በተጨማሪም ከሌላው አማኝ ጋር በሕብረት ከመቼውም የበለጠ መያያዝ እንዳለበት ለመገንዘብ።

1. ከቁ.1-2 የሙሴ ሕግ አምሳያነቱና የማያደርገው ነገር ምንድነው?

2. ቁ.3 የኮርማዎችን የፍየሎች ደም ኀጢአትን የማያስወግደው ለምንድነው?

3. ከቁ.5-9 ክርስቶስ መሥዋዕት ሊሆን ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ለምንድነው?

   - ኢየሱስ እራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበው እንዴት ነው?

   - ይህ ፈቃድን ለእግዚአብሔር ስለ መስጠት እንዴት እንደሆን ያስተምረናል?

4. ቁ.10,12,14, ተደጋግሞ የተገለፀው “አንድ ጊዜ” የሚለው ቃል ከብሉይ ካህናት የተለየ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?

5. ከቁ.11-12 የብሉይና የአዲስ ኪዳን ካህናትን አገልግሎት እንዴት ያወዳድራቸዋል?

6. በቁ.10,12 መሠረት የክርስቶስ መሥዋዕትነት በሰዎች ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድነው?

7. ከቁ.15-18 መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክረው ምንድነው?
   - ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ኀጢአታቸውን ደግሜ አላስብም ሲልስ?

8. ከቁ.19-20 ክርስቶስ የመረቀልን መንገድ ምን አይነት ነው?

   - መጋረጃውንና ሥጋውን ያመሳሰለበት ምክንያት ለምንድነው?

9. ከቁ.21-22 ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንዲቀርቡ ነው የሚመክራቸው?

10. ከቁ.23-25 እርስ በርስ ስላላቸው ግኑኝነት የሰጣቸው ምክር ምንድነው?

- የእርስ በርስ መተያየት ውጤት ምንድነው?

12. በዚህ በመጨረሻው ዘመን ምን ማድረግ እንደሚገባን ይህ ክፍል ያስተምረናል?

## <u>ጥናት አስራ አንድ</u>

## <u>ድፍረትህን አትጣል</u>

<u>**የምንባብ ክፍል ዕብ. 10፡26-39**</u>

<u>*መግቢያ፡-*</u> ቅዱሳን በጌታ ያላቸውን ተስፋና ድፍረት እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው የተፃፈውን ክፍል እንመለከታለን።

<u>*ዓላማ፡-*</u> የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርገን የተሰጠንን የተስፋ ቃል እንድናገኝ መፅናት እንዳለብን ለመገንዘብ

1. ከቁ.26-27 የሚያስጠነቅቃቸው ስለምንድነው?
2. ቁ.28 የሙሴን ሕግ የናቀ የሚጠብቀው ፍርድ ምንድነው?
3. ከቁ.29-31 የእግዚእብሔርንስ ልጅ የረገጠ ምን ይጠብቀዋል?
    - ይኼኛው ቅጣት ከባድ የሚሆንበት ዋነኛው ምክንያት ለምንድነው?
4. ቁ.32 ቅዱሳኑ በምን ውስጥ እያለፉ እንደሆነ ነው የሚነገረን?
5. ቁ.33 አስቡ ብሎ የሚነግራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
    - የቀደመውን ነገር ማሰባቸው አሁን ለሚያልፉበት ችግር ምን ይጠቅማቸዋል?
6. ቁ.34 ከዚህ ቀደም ያደረጉትን ነገር መልሶ የሚያስታውሳቸው ለምንድነው?
7. ከቁ.35-36 የሚመክራቸውና የሚያስጠነቅቃቸው ስለምንድን ነው?
    - ለእኛ በጌታ ላይ ድፍረት የምንለው የቱን ነው?
    - የተስፋውን ቃል እንድናገኝ ማድረግ የሚገባን ነገር ምንድነው??
8. በቁ.37-38 መሠረት የሚመጣው ምንድነው?
    - ፃድቅ የሚኖረው በምንድነው? ምንስ ማለት ነው?
    - እግዚአብሔርስ ደስ የማይሰኘው በማን ነው?
9. ይህ ክፍል በእምነት የመኖር ውጤት ምን እንደሆነ ያስተምረናል?
10. በመከራ ውስጥ ብንሆንም ምን ማድረግ እንደሚገባን ክፍሉ ያስተምረናል?

# ጥናት አስራ ሁለት

# የተመሰከረለት እምነት

**የምንባብ ክፍል** ፡- ዕብራዊያን 11፥1-16

**መግቢያ**፡- እግዚአብሔር እስከ አሁን ድረስ በእምነታቸው ስለሚመሰክራላቸው የእምነት አባቶች የተፃፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ**፡- እግዚአብሔርን ካለ እምነት ደስ ማሰኘት እንደማይቻልና፡ በእምነት መኖር ስንል ምን ማለት እንደሆነ ለመገንዘብ፣

1. በቁ.1 ላይ እምነት ያለውን ሁለት ተግባራት ግለፅ?
   ከ2-3 ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ የሚታወቀው እንዴት ነው?
2. ቁ.4 የአቤልን መሥዋዕት ከቃየል ይልቅ እግዚአብሔር የተቀበለው ምክንያት ለምንድነው?
3. እኛስ የምናቀርበው ስጦታ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው እንዴት ስናቀርበው ነው?
4. ቁ.5 ሄኖክ ሞትን ሳያይ እንዲወሰድ ያደረገው ምክንያት ምንድነው?
   - ይህ ስለ ሄኖክ ሕይወት ምን ያስተምረናል?
5. በቁ.6 ላይ እግዚአብሔርን ለማስደስት ሰው ማወቅና መረዳት ያለበት ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?
6. በቁ.7 ኖኅ እግዚአብሔርን ማመኑን የተገለፀበት መንገድ እንዴት ነው?
   - ከኖኅ ስለ ትዕግስት የምትማረው ምንድነው?
7. ቁ.9 አብረሃም ተለይቶ ወደማያውቀው ምድር እንዲሄድ ያደረገው ምክንያት ምንድን ነበር?
8. ከቁ. 9-10 አብረሃምና ልጆቹ እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ኪዳን እንዴት ነበር የጠበቁት?
9. አንተስ እግዚአብሔር በእንዴት ያለ ሁኔታ መጠበቅ እንዳለብህ ይህ ክፍል ያስተምርሃል?
10. ከቁ.11-12 ሣራ በእርጅናዋ ዘመን ልጅ ለመፀነስ የቻለችው እንዴት ነው?

11. ከቁ.13-16 አምነው ነገር ግን ተስፋቸውን ሳይወርሱ ስላለፉት ምን ያስተምርሃል?
    - ተስፋ በላይ እንዳለህ ማወቅህ በእምነትህ ጸንተህ እንድትቆም እንዴት ይረደሃል ?

12. በቁ.16 ላይ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ እንዲጠራ ያላፈረው ለምን ይመስልሃል?

13. ከላይ የተዘረዘሩት የእምነት አባቶች ስለ እምነታቸው እግዚአብሔር መስክሮላቸዋል።

    - አንተስ በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ምን ማድረግ እንዳለብህ ይህ ጥናት ያስተምርሃል?

## ጥናት አስራ ሦስት

## ታላቅ መሥዋእትን መክፈል

**የምንባብ ክፍል፡-** ዕብራዊያን 11፡17-31

**መግቢያ፡-** እግዚአብሔር እስከ አሁን ድረስ በእምነታቸው ስለሚመሰክራላቸው የእምነት አባቶች የተፃፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን ካለ እምነት ደስ ማሰኘት እንደማይቻልና፡ በእምነት መኖር ስንል ምን ማለት እንደሆነ ለመገንዘብ፣

1. ከቁ.17-19 አብረሃም አንድ ልጁን ይስሐቅን እስከ መሠዋት ድረስ እንዲታዘዝ ያስቻለው ምክንያት ምን ነበር?
    - በአንተስ ሕይወት ፍፁም መታዘዝ ይታይብሃል?
    - ካልሆነስ ለምን ይመስልሃል?
2. ቁ.20 ይስሐቅ ልጆቹን በእምነት ባረካቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ቁ.21 ላይ ያዕቆብ ያደረገው ምንድነው?
    - ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች መባረኩ ከእምነት ጋር ምን ያገናኘዋል?
4. በቁ.22 መሠረት የዮሴፍ እምነት ምን ነበር?
    - ዮሴፍ አጥንቱን ይዘው እንዲሄዱ መናገሩስ ከእምነት ጋር ምን ያገነኘዋል?
5. የሙሴ ወላጆች የንጉሱን አዋጅ ሳይፈሩ ሙሴን ለሦስት ወር ለመደበቅ ያስቻላቸው ምንድን ነበር?
    - መፍራትና ማመን ልዩነታቸውና ውጤታቸው እንዴት ነው?
6. ከቁ.24-28 ስለ ሙሴ የተጻፈውን በመመልከት
    - እንቢ ያለው ምንድነው?
    - ከቁ. 25-26 የመረጠው ምንድነው?
    - ከቁ. 25-27 የተመለከተው ምንድነው?

- ቁ.28-29 ያደረገው ምንድነው?

7. ሙሴ ሁሉን እንቢ ብሎ አግዚአብሔርን የታዘዘው ምንን በመመልከቱ ነው?

    - ስለዚህ እኛስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና ለመጽናት ምን ማድረግ ያለብን ይመስልሃል?

8. ቁ.30 መሠረት የኢያሪኮ ቅጥር የወደቀበት ምክንያት ምንድነው?

9. ቁ.31 ጋለሞታይቱ ረዓብ የእምነት ሴት ያስደረጋት ምንድነው?

10. በዚህ ጥናት መሠረት እምነት ብለን ስንል ምን ማለታችን ነው?

    - በእምነታችን ጸንተን ለመቆም እንድንችል ይህ ጥናት ምን ያስተምረናል?

    - ሁልጊዜ በሕይወታችን አርቀን ልናየው የሚገባን እውነት ከክፍሉ የተረዳኸው ምንድነው?

## ጥናት አስራ አራት

## የእምነት አርበኞች

**የምንባብ ክፍል፡-** ዕብ. 11፡32-40

**መግቢያ፡-** እግዚአብሔር እስከ አሁን ድረስ በእምነታቸው ስለሚመሰክራላቸው የእምነት አባቶች የተፃፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን ካለ እምነት ደስ ማሰኘት እንደማይቻልና፡ በእምነት መኖር ስንል ምን ማለት እንደሆነ ለመገንዘብ፣

1. በቁ.32 ላይ ፀሀፊው "እንግዲህ ምን እላለሁ" ሲል ምን ለማስገንዘብ ይመስልሃል?

2. ከቁ. 33-34 መሠረት በእምነት ያደረጉት ምንድነው?

   - እነዚህ የእምነት ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነማንን ይመስላሉ ብልህ ትገምታለህ?

3. ከቁ. 35-38 መሠረት ስለ እምነት አርበኞቹ የተጠቀሰው ምንድነው?

4. ከቁ.33-34 እና በቁ.35-38 ያለው ልዩነትና ተመሳሳይነት እንዴት ነው?

5. ከቁ.39-40 በእምነታቸው የተመሰከረላቸው ቅዱሳን ያለ እኛ ፍፁም እንዳይሆኑ ያደረጋቸው ምክንያት ለምንድነው?

6. በእምነት ማሸነፍ ብለን ስንል በዚህ ክፍል መሠረት ምን ማለታችን ነው?

7. ዛሬስ ላለነው አማኞች በእምነት ምክንያት ልናልፍበት ስለ ምንችልበት የሕይወት መንገድ ምን ያስተምረናል?

8. አንተስ ስለ እምነትህ ዋጋ መክፈልና እሰከ ምን ድረስ ለመክፈል መዘጋጀት እንዳለብህ ይህ ክፍል ያስተምርሃል?

## ጥናት አስራ አምስት

## በሕይወታችን እንዳንዝል…

**የምንባብ ክፍል፡- ዕብ12፡1-29**

*መግቢያ፡-*

ሰው በሥጋ ሰውነቱ ከስራ ብዛት ወይም ከእረፍት ማጣት እና ከሌሎች ነገሮች የተነሳ ሊደክምና ሊዝል እንደሚችል ሁሉ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱም ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ሊያደርግ ካልቻለ ይዝላል። በዛሬው ጥናታችን ክርስቲያን በመከራም ይሆን በምቾት ጊዜ ሳይዝል ፀንቶ እንዴት እንደሚችል እናያለን።

*ዓላማ፡-*

አንድ ሰው በሕይወት የሚገኘው ፈታኝ ነገሮች ቢኖሩም፣ እንደ ክርስቲያን ደግሞ ሕይወትን ሊያዝሉ የሚችሉትን ነገሮች ሁሉ ተቋቁመን ታማኝ ሯጭ እንድንሆን ለማበረታታት፣

1. አንድ ጊዜ በጌታ ብርቱ የነበረ በኋላ ግን ለመንፈሳዊ ነገር የነበረው ትጋት እና ጥማት ጠፍቶ የራቀ( የሸሸ) ሰው የምታውቅ ከሆነ፣ ለቡድንህ አካፍል።

    - ለድካሙ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድን ነበረ?

2. ከቁ.1-2 መሠረት ይህ መልዕክት የተጻፈላቸው የዕብራዊያን ሰዎች በምን ዓይነት ሕይወት ውስጥ ያሉ ይመስሉሃል?

    - በብርታት ወይስ በድካም ነው ያሉት?

3. ቁ.3 የዕብራዊያን ሰዎች ከዚህም አልፈው ይበልጥ እንዳይደነዝዙ ፀሐፊው የሰጣቸው አንደኛው ምክር ምንድነው?

4. በቁ.3 ከኃጢአተኞች በደረሰበት መከራ ውስጥ ፀንቶ የቆመውን ጌታ ማሰባቸው በሕይወታቸው እንዳይዝሉ እንዴት ሊረዳቸው ይችላል?

5. በቁ.1-2 መሠረት እነዚህ በሕይወታቸው እየደከሙ ያሉ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን እንዲመለከቱ ለምን የታዘዙ ይመስልሃል?

    - ለእኛስ ለሕይወታችን ፈታኝ የሆኑ መከራዎች ሲገጥሙን ክርስቶስን አሻግሮ በማየት እንዴት ከጥፋት ልንድን እንችላለን?

6. ከቁ. 4-6 ባለው መሰረት የመልዕክቱ ፀሐፊ በሕይወታቸው እንዳይዝሉና እንዳይጠፉ የሰጣቸው ሌላ ምክር ምንድነው?

7. ከቁ. 7-11 መሰረት የእግዚአብሔርን ቅጣት ሰዎች መታገስ ያለባቸው ለምንድነው?

8. በሰው ሕይወት የሚመጣ መከራ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቅጣት ነው ወይስ በሌላም ምክንያት መከራ ሊመጣ ይችላል?

9. ከቁ.1-2 ያለው እንዲሁም ቁ.10-11 ያለውን በመደገፍ በመከራ ታግሶ የመጠበቅ ውጤት ምንድነው?

10. ከቁ. 14-17 ፀሀፊው ሌላ ሶስተኛ የሚሰጠው ምክር ምንድነው?
    - በዚሁ ክፍል ውስጥ ለዓለም የሚመች ሰው ምን ማለት ነው?
    - ፀሐፊው ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያስ ለምን የሰጠ ይመስልሃል?

11. ከዓለም የሚመች ሰው ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? ብለህ ታሰባለህ? በእኛ ሕይወት ውስጥስ ደካማነት እና በመንፈስ መዛልን እንዴት ሊመጣ ይችላል?

12. በዚህ ባነበብነው ክፍል መሰረት ክርስቲያን በሕይወት ዝሎ እንዳይወድቅ የተሰጡት ሦስት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

13. በቁ.18 ላይ "አልደረሳችሁም" ሲል በቁ. 22 እና 24 ላይ "ደርሳችኋል" የሚሉ ቃላቶች አሉ?
    - " አልደርሳችሁም" እና "ደርሳችኋል" ሲል ምን ማለቱ ነው?
    - የት ነው የደረስነው የትስ ነው ያልደረስነው?

14. በብሉይ ወደ እግዚአብሔር ተራራ የደረሱት ሰዎች ፈርተው ከተንቀጠቀጡ፣ ዛሬ የእግዚአብሔር እውነት ገብቷቸው ወደ ኢየሱስ የደረሱ ሰዎች ዝለው ጌታን ቢተዉ እንዴት ወዳለ የሚያስፈራ ነገር ውስጥ የሚገቡ ይመስልሃል?

15. ከቁ.26-29 ባለው ክፍል በመደገፍ በጌታ ፀንተውና በርትተው የሚኖሩስ ሰዎች ምን አይነት ዕጣ ይደርሳቸዋል ብለህ ታስባለህ?

# ጥናት አስራ ስድስት

# ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖረን....

**የምንባብ ክፍል፡- ዕብ 13፡1-24**

***መግቢያ፡-***

ክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን በሁሉ ነገሮች ረገድ ያለው ሕይወት የተመጣጠነ እና ጤነኛ ሊሆን ይገባል። ለወገኖች፣ ለሀብት፣ ለቤተክርስቲያን መሪዎች፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ራሱ ያላቸው አመለካከት እና ሕይወት ጤነኛ ሊሆን ይገባል። በዛሬው ጥናታችን የዕብራዊያን ፀሐፊ ይህንን አስመልክቶ ለመጽሐፉ መደምደሚያ የሰጠውን ክፍል እንመለከታለን።

***ዓላማው፡-***

እንደ ክርስቲያን ለሰዎች፣ ከአገልጋዮች እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት አልፎም ለሀብት፣ ለመፅሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ያለን አመለካከት እንዴት መሆን እንዳለበት መጠቆም።

1. በቁ.1 ላይ እርስ በእርስ እንድንዋደድ ካዘዘ በኋላ ቀጥሎ ባሉት 3 ቁጥር በምን አይነት መልኩ መዋደድ እንዳለብን ይዘረዝራል።
   - ስለ እንግዶች?
   - መከራ ስለሚቀበሉ ሰዎች?
   - ስለ ትዳር ጓደኛሞች?
2. ከ1-4 የተዘረዘሩት ትዕዛዞች የሰውን ፍቅር ሊገልጹ እንዴት ይችላሉ?
   - አንተስ ለሌላ ሰው ያለህን ፍቅር በምን ማሳየት ትችላለህ?
3. በቁ.5 ላይ ለገንዘብና ለሃብት እንዴት ያለ አመለካከት እንዲኖረን ነው የሚመክረን?
4. በቁ. 5-6 "ያለን ይበቃናል" ብለን ገንዘብን ባለ መውደድ እንድንኖር የተመከርነው እንዴት ነው?
   - ፀሐፊው ከብሉይ ኪዳን የጠቀስነውን ጥቅስ አስተውል! ለምን ይመስልሃል?
5. ቁ.7 የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና የቃሉ አስተማሪዎች ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዴት እንድንኖር ነው የሚመክረን?

- ፀሐፊው ለምን ምክንያት ነው ለዋኖቻችን (ለመሪዎች) እንድንገዛ የሚመክረን (በቁ.17 ላይ የተሰጠውን ምክንያት ተመልከት)

6. ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዳንዴ ትዕዛዝ ሲተላለፍ ሰዎች የማይታዘዙበት ምን ነገር አይተህ ተውቃለህ?

   - በዚህ ክፍል መሠረት ምን መደረግ አለበት ትላለህ?

7. የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በተመለከተ በቁ. 9 ላይ የተሰጠው ምክር ምንድነው?

   - " እንግዳ ትምህርቶች" ማለት ምን ማለት ነው? (ገላ1፡8-9 እንዲሁም 2ኛ ቆሮ 11፡3-4 ያለውን ተመልከቱ)

   - የስህተት ትምህርት ሲመጣስ በምን እናውቃለን?

8. በቁ.15-16 ባለው መሠረት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙት የተዘረዘሩት ነገሮች ምንድን ናቸው?

9. በቁ.16 ለሌሎች ማካፈል እግዚአብሔር ደስ እንደሚያሰኙት ከተጠቀሱት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው።

   - በቁ.5 ላይ ገንዘብን ስለመውደድ እና ያለኝ ይበቃኛል ስለማለት ከተሰጠው ክፍል ጋር እንዴት ሊገናኝ ይችላል?

10. እግዚአብሔርን ከሚያስደስቱት ነገሮች ውስጥ ከክፍሉ የተማርከው ምንድነው?

11. ለሌሎች ሰዎችና ለመሪዎች ያለንን ፍቅር የምንለካበት ሚዛን ከክፍሉ የተረዳኸው ምንድ